# ኤጀንሲው የመረጃ አቀባይነት ሚናውን አጠናክሮ ይቀጥላል

ያለንበት ዘመን የመረጃ ሃያልነት የተረጋገጠበትና መረጃ ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጥበት ወቅት ሆኖ ተገኝቷል። ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወተው መረጃ እንደሆነም ከተረጋገጠ ውሎ የአደረ ጉዳይ ነው። በመረጃ አቅርቦትም ረገድ ቤተመጻሕፍት ቤተ መዛግብትና የዶክመንቴሽን ማዕከላት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

ከዚህ አንጻር ከዛሬ 65 ዓመታት በፊት የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር በሚል ስያሜ የተቋቋመው የዛሬው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ የሀገሪቱን የመረጃ ሃብቶች በማሰባሰብ በማደራጀትና እየተንከባከበ በመጠበቅ በትምህርት በጥናትና ምርምር እንዲሁም በፈጠራ ሥራ ለተሠማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ተመራማሪዎች ደራሲያንና የጥናትና ምርምር ተቋማት የቅርብ አጋር በመሆን ትናንትም ሆነ ዛሬ በማገልገል ላይ ያለ ተቋም ነው።

ተቋሙ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ ሲቋቋም ዓላማ ያደረገው የሀገሪቱን የመረጃ ሀብቶች በማሰባሰብ በማደራጀትና ጠብቆ በማቆየት ለጥናትና ምርምር በማዋል ለትውልድ ማስተላለፍ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የቴክኖሎጂና ዘመናዊ አሠራርን በመከተል የመረጃ ሃብቶች ለሀገር ልማት ውለው መረጃ ፈላጊዎችንና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ቀደም ሲል በቤተመጻሕፍት አገልግሎት ሲጠቀምበት የነበረውን አሮጌ ህንጻ በማደስና በቅርቡም መንግስት በመደበለት ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ አዲስ ዘመናዊ ህንጻ በማስገንባት ለተጠቃሚዎችና ለህብረተሰቡ አገልግሎቱን በስፋትና በተመቻቸ ሁኔታ በመስጠት ላይ ነው።

ኤጀንሲው በአዋጅ ከተሰጡት ሥልጠናና ተግባራት መካከል ከሀገር ዓቀፍና ዓለም ዓቀፍ አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ የቤተመጻሕፍትና የቤተመዛግብት ሙያ እንዲያድግና እንዲስፋፋ የትብብር ስምምነት በመፍጠር አቅሙን ማጐልበት በመሆኑ በመስኩ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው ከቱርክ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት፣ ከፈረንሳይ ብሔራዊ ቤተመጻሕፍትና ብሔራዊ ቤተመዛግብት፣ ከዩኔስኮ፣ ከአለም አቀፍ ቤት መጻሕፍት ማህበር፣ ከአለም አቀፍ ቤተመዛግብት፣ ከዓለም ባንክና ከመሳሰሉት ድርጅቶች ጋር የተለያዩ የፕሮጀክት ጥናቶችን በማካሄድና ተሳታፊ በመሆን በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

በቅርቡም በቤተመጻሕፍት ዘርፍ ፈጣንና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የተጠቃሚዎችንና የህብረተሰቡን ፍላጐት ማርካት እንዲቻል ከብሪቲሽ ካውንስል ጋር የፕሮጀክት የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ዝግጅቱን አጠናቆ ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በጋራ ያደራጀውን ቤተመጻሕፍት አስመርቆ በማስከፈት የቤተመጻሕፍት አገልግሎት ሥራውን አጠናክሮ ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲና ብሪቲሽ ካውንስል ለበርካታ አመታት በዘርፉ ብዙ ልምዶችን ያካበቱ በመሆናቸው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በጋራ በመጠቀም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ትርጉም ያለው ድርሻ ማበርከት እንደሚቻል ከወዲው ይታመናል።